# ኢህአሰ ከዳሉል በረሀ እስከ ደጀን

ጊዜው እየረዘመ ሲሄድ የምናስታውሳቸው ድርጊቶች ያሳለፍንባቸው ቦታዎች ወቅቶች ይረሳሉ።

ዛሬ ተገናዕተን እንደምናወራው ቀላል አይሆንም ፤ ምስክሮች እየጠፉ ይሄዳሉ ። አሁን ላለነው ለተሳተፍንበትም ሆነ ላልተሳተፍንበት በተገናዐንበት ወቅት እያነሳን ስናወራው የሂሊና መዝናዓ ወጌሻችን ነው ። ከዚህ በላይ ግን ትምህርት ተማርንበት ብዬ ለማለት ግን ያስቸግረዓል። የሚያስታውሰዕ ነገር ቢኖር 1973 ዓም የኢህአሰ ሰራዊት በከፍተዓ ደረጃ በተበተነበት ወቅት ወደ ማህል አገር በዛ ያሉ የሠራዊቱ አባሎች ገብተው ነበር። ከነዚህም መካከል ጥቂቶቹ አንድ ቀን በአዲስ አበባ ከተማ አራት ኪሎ ህብረት ሆቴል ውስጥ ቁጭ ብለን ቡና እየጠጣን ያሳለፍነውን ስናወራ ቆየንና ወደ መጨረሻ ላይ አንዱ ከማህላችን << መቼም ተማርን >> ብሎ አስተያየቱን ሲሰጥ እንግዳ ቀበል አድርጎ አተኩሮ እየተመለከተው << ለመቼ?>> ብሎ ሲጠየቀው ሁላችንም ስቀን ቀላልደን ተለያየን።

አሁንም ምናልባት ለዓ ትምህርታዊ ብለን ባንወስደውም ፤ ለሚቀጥለው ትውልድ ትምህርት ይሆናል። መጪው ትውልድ ስህተት የተሰራውን አርሞ ትክክል የተሰራውን አጠንክሮ እንዲገፋበት ይረዳዋል።

በሀገሪቷ ዲሞክራሲያዊ ስርአት ሰፍኖባት ፦ ህዝቡ በዲሞክራሲ በእምነት በፍቅር መተሳደር ሲጀመር ፖሊቲካውና አስተዳደሩን ለጥቂት ባለሞያዎች ሲቃወሙ ልጆች እንደ ተስፋዬ ደበሳይ ፤ አብዲሳ አጋ ፥ ቼጉቬራ፦ ኔልሰን ማንዴላ ፤ ማህተመ ጋንዲ ፤ እሆናለሁ የሚለውን ቀይረው እንደ ቢል ጌት ፤ እሆናለሁ ብለው ማሰብ  እስኪጀምሩ ትምህርታዊ ይሆናል። በዚህ አጋጣሚ የተቻላቸውን ጽሁፍ ያበረከቱትን ክፍሉ ታደሰ (The Generation ) እና ያ ትውልድ በአማርዓ ፤ ተራሮችን ያንቀጠቀጠ ትውልድ ፤ እሰየው አበጃችሁ ጨምሩበት እላለሁ።

ስድስት ሚሊዮን አይሁዶች ያለቁበት the holocost ብዙ ትዕይንተ (movies) ተሰርተውበታል፤ ብዙ መጻህፍት ተጽፌውበታል። የአገራችን አብዮት በስታስቲክ የተያዘ ስድስት ሚሊዮን ህዝብ አለቀበት ባይባልም በጣም ብዙ ህዝብ አልቆበታል፤ በየሐገሩ ተሰደዋል፤ ወጣቶች እንደ ሾላ ረግፌዋል። ከነዚህም ከአዲስ አበባ እስር ቤት ከነበሩት ወጣቶች ውስጥ ደርግ በድሮው ኢላማ መተኮሻ አካባቢ አስር ኪሎሜትር ከመሀል ከተማ ርቀት ብረት ፋብሪካ ከመድረሱ በፊት በሚገዐው ተራራr ስር የረሸናቸው ከ500በላይ ናቸው ። ከነዚህም ምስክር የሚሆን ከርሸናው ያመለጡት ውስጥ  ቦገን እና ማርቆስ በይህይወት ምስክሮች ናቸው።  በቀይ ሽብር በየመንገዱ እየተገደሉ ተጥለው አስከሬናቸውን እንዳያነሳ ተከልክሎ ለመቀጣጫ ይሆናል እየተባለ አስከሬናቸውን  ጸሃይ ላይ ተሰጥቶ የዋለው በየክፍለ ሀገሩ ከተሞች ያለቁትን ቤት ይቁጠረው ብዬ ለታሪክ ፀሀፊ እተወዋለሁ።

በዚህ ትንሽ ጽሁፍ እስከዛሬ ድረስ የምናውቃቸውን ጀግኖች ሁሉ የሰሩትንና ያደረጉትን ማቅረቡ አስቸጋሪ ይሆናል። ሆኖም የተቻለውን ያህል ከዚያም ከዚህ ማቅረቡ በጊዜው የነበረውን የተዘበራረቀ ሁኒታ በዜና መልክ ማካፈል ትምህርታዊ ይሆናል ብዬ አምናለሁ።

ለዲሞክራሲ፣ ለህዝብ ስልጣን ካበረከቱት ውስጥ የነደጃዝማች ታከለ ወልደ ሃዋርያ በጣሊያን ወረራ ወቅት በአርበዕነት የተዋጉትን አርበዖችን የብዙ ህዝብ ፊርማ ሰብስበው ኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት የሪፓብሊክ አስተዳደር እንጂ የዘውድ አምባገነናዊ መንግስት አትፈልግም ብለው ለተባበሩት መንግስታት (League of Nations) የላኩ፤ 1953 ዓም btaheሳስ ግርግር የሃይለ ስላሴን መንግስት ለመጣል ከተዋጉት ጄነራል መንግስቱ ንዋይ ፥ ገርማሜ ንዋይ፥ ኮረኔል ወርቅነህ እና እንዲሁም ሌሎች የክብር ዘበዓ ሰራዊትና ፤ ሌሎችም በየጊዜው ያደረጉትን አስተዋጽዖ ልንዘነጋው አይገባም።

አሁንም በደረስንበትና ባሳለፍነው ትውልድ ከወደሗላ የሃይለስላሴ መንግስት እስከ አሁን ባለንበት ወቅት ትግሎች ተካሂደዋል። ብዙ ጀግኖጽም ተወልደው አድገው በቅን ልቦና በጀግንነት ተሰውተዋል።

*ትግሉ በጥቄት ህዝብ በየቦታው ብቅ ጥልቅ ከማለት አልፎ እየረቀቀና አገር አቀፍ እየሆነ በድርጅት ተቀነባብሮ ተካሂዶአል ።*
*ከድርጅቶችም አንዱ ብዙ ህዝብ ያቀፈው ኢህአፓ ነበር። ኢህአፓ ከፍተዓውን የወጣት ክፍል ሰራተዓውን ፤ አርሶ አደሩን ፤ ወታደሩን በተለይ የአየር ወለዱን ክፍል ያቀፈ ድርጅት ነበር።*
*የኢህአፓ ሰራዊት (ኢህአሠ) ከዝቅተዓው የኢትዮጵያ መሬት ከዳሉል በረሁ እስከፍተዓው የሰሜን ተራሮች በነራስ ደጀን ላይ ተንቀሳቅሶአል፤ ተዋግቷል፤ ብዙ መስዋዕትነት ከፍሎአል። የነጻነት ተስፋ ችቦውን አብርቷል፤ ባንዲራውን አውለብልቦአል። ዛሬ ይህ ድርጅት ከጠረፍ እስከ ጠረፍ፤ ከዳሉል እስk ደጀን ተስፋፍቶ የነበረ ትግሉን አቀነባብሮ የመራ፤ ምን አኮላሸው? who dropped the ball የሚለው ለብዙ ህዝብ እንቆቅልሽ ነው።*
*ምናልባት በቁጥር ይሄን ያህል ታጋዮች አስረክበንህ ነበር ፤ ምን ሰሩ፤ ምን አበረከቱ፤ የት ደረሱ፤ ምን ጠፋ፤ ምን ስህተት ተሰራ ብሎ የሚጠይቀው ማነው ብንል መልሱን ማግዐት ያስቸግራል ። ሆኖም ጠያቂው አሁንም ወደፊትም ህዝብ ነው ትውልድ ነው መልሱን የያዘ ሁሉ ወደፊት እንዲሚቀርብ ተስፋ አለን።*

*ይቀጥላል*